# ከመጥፎ ጓደኛ ራቅ!

**መመሪያ፦** ይህን መልመጃ ጸጥታ በሰፈነበት ቦታ ሆነህ ሥራ። ጥቅሶቹን ስታነብ በቦታው እንዳለህ አድርገህ አስብ። ሁኔታውን በዓይነ ሕሊናህ ለመሳል እንዲሁም በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሱት ሰዎች ሲነጋገሩ ድምፃቸውን ለመስማትና ስሜታቸውን ለመረዳት ሞክር። ታሪኩ ሕያው እንዲሆንልህ አድርግ።

**ዋነኞቹ ባለ ታሪኮች፦** ዲና፣ ሴኬም፣ ያዕቆብ፣ ስምዖንና ሌዊ

**ታሪኩ በአጭሩ፦** ሴኬም ዲናን በዖታ አስነወራት፤ ከዚያም በሁኔታው የተናደዱት ወንድሞቿ የበቀል እርምጃ ወሰዱ።

## ❶ *ሁኔታውን ለማስተዋል ሞክር።—ዘፍጥረት 34:1-31ን አንብብ።*

ዲና በከነዓን ካሉት ጓደኞቿ ጋር ስትገናኝ ምን ታደርግ የነበረ ይመስልሃል? ______________________

______________________

______________________

ሴኬም ዲናን ‘በጣፈጠ አንደበት ለማናገር’ ምን ዘዴ የተጠቀመ ይመስልሃል? ______________________

______________________

______________________

በቁጥር 30 ላይ በተገለጸው መሠረት ያዕቆብ፣ ስምዖንንና ሌዊን ሲቆጣቸው በአነጋገሩ ላይ ምን ዓይነት ስሜት ሲንጸባረቅ ይታይሃል? ______________________

______________________

______________________

## ❷ *ጥልቅ ምርምር አድርግ።*

ዲና ከከነዓን ሴቶች ጋር ጊዜ ለማሳለፍ ሁልጊዜ ትሄድ የነበረው ለምን ይመስልሃል? (ለምሳሌ ያህል፣ እሷም ሆነች እነሱ የሚወዱት አብረው ሊያደርጉት የሚችሉት ነገር ምን ሊሆን ይችላል? ቤቷ ስትሆን የማታገኘው ከነዓናውያን ጋ ስትሄድ ግን የምታገኘው ነገር ምን ሊሆን ይችላል?) ______________________

______________________

______________________

ዲና፣ ሴኬም ምን ጥሩ ጥሩ ባሕርያት እንዳሉት ተመልክታ ሊሆን ይችላል? (*ቁጥር 3, 12, 19ን በድጋሚ አንብብ።*) ______________________

______________________

መጽሐፍ ቅዱስ ዲና ከሴኬም ጋር የፆታ ግንኙነት መፈጸም እንዳልፈለገች የሚጠቁመው እንዴት ነው? (ቁጥር 2ን በድጋሚ አንብብ።)

ስምዖንና ሌዊ በሴኬም ከተማ የሚኖሩትን ወንዶች በመግደል መበቀላቸው ትክክል ይመስልሃል? ከሆነ ለምን? ካልሆነስ ለምን?

**3** ***ከዚህ ታሪክ ያገኘኸውን ትምህርት ተግባራዊ አድርግ። ከዚህ በታች ስለተዘረዘሩት ነገሮች ምን ትምህርት እንዳገኘህ ጻፍ፦***

ጓደኞችህን በጥበብ ስለ መምረጥ።

የእውነት የሚያናድድ ነገር ቢያጋጥምህም እንኳ ራስን ስለ መቆጣጠር።

***ልትሠራበት የሚገባ ተጨማሪ ነገር።***

ለአምላክ የሥነ ምግባር ደንቦች ምንም ግድ የሌላቸው ሰዎች አባብለው የፆታ ብልግና እንድትፈጽም እንዳያደርጉህ ምን ማድረግ ትችላለህ?

**4** ***ከዚህ ታሪክ ውስጥ ልብህን ይበልጥ የነካው ምንድን ነው? ለምንስ?***



www.jw.org © 2011 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania